- ምክንያቱም የኃጢአት ዋጋ የሚከፈለው በኃጢአተኛው ሞት ስለሆነ ነው።

- ንጉሥ ሰሎሞን ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ምን ደረሰባቸው?

- እስራኤላውያን ቀጣዩ ንጉሥ ማን መሆን እንዳለበት አልተስማሙም ነበር።

- ስለዚህ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ተከፍለው ሁለት ሕዝቦች ሆኑ።

- በሰሜን የሚገኙት ዐሥሩ ነገዶች በደቡብ ከሚገኙት ሁለት ነገዶች ተለዩ።

- በሰሜን የነበሩት ዐሥሩ ነገዶች ምን ተብለው ተጠሩ?

- እስራኤል።

- በደቡብ የነበሩት ሁለት ነገዶች ምን ተብለው ተጠሩ?

- ይሁዳ።

- ብዙ ነገሥታት በእስራኤል ላይ ገዢ ነበሩ፤ በይሁዳ ምድር ብዙ ነገሥታት ገዝተዋል።

- አብዛኛዎቹ ነገሥታት በእግዚአብሔር ያላመኑ ነበሩ።

- ጥቂቶቹ ነገሥታት ብቻ በእግዚአብሔር ያመኑ ነበሩ።



# ትምህርት 39

1. እግዚአብሔር በሙሴ ምትክ የመረጠው አዲሱ መሪ ማን ነበር?

ሀ- ኢያሱ።

2. እግዚአብሔር ቃሉን በመጠበቅ ለአብርሃም ዘሮች የከነዓንን ምድር አወርሷቸዋል?

ሀ- አዎን።

3. ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

ሀ- ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመተው በጣም ክፉዎች ሆኑ።

ለ- ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ጣዖት ሠርተው በእግዚአብሔር ፈንታ አመለኩአቸው።

4. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመተው ጣዖቶችን እንዲያመልኩ ያሳታቸው ማን ነበር?

ሀ- ሰይጣን።

5. እኛ ከእግዚአብሔር ሌላ የምናመልከው ነገር ካለን ማንን እያመለክን ነው?

ሀ- ሰይጣንን።

6. ሰይጣን ሰዎች ጣዖትን እንዲያመልኩ የሚያደርገው ለምንድን ነው?

ሀ- ሰይጣን እግዚአብሔርን ስለሚጠላ ማንም እርሱን እንዲያመልክ ስለማይፈልግ ነው።

ለ- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላ እግዚአብሔር ማንንም እንዲያድን አይፈልግም።

7. እስራኤላውያን ጣዖት በማምለካቸው እግዚአብሔር በምን ቀጣቸው?

ሀ- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ጠላቶች መጥተው ሰብሎቻቸውን ሁሉ እንዲያጠፉ አደረገ።

ለ- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ጠላቶች መጥተው ከብቶቻቸውን እንዲዘርፉ አደረገ።

ሐ- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ጠላቶች መጥተው እስራኤላውያንን ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አደረገ።

8. እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ተናዝዘው እግዚአብሔር እንዲያድናቸው በሚለምኑበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ምን ያደረግ ነበር?

ሀ- እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ተናዝዘው እግዚአብሔር እንዲያድናቸው በሚለምኑበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን መካከል የሚመሯቸውን ወንዶችና ሴቶችን እየመረጠ ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ያደርግ ነበር።

9. እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ይመሯቸው ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣቸው ወንዶችና ሴቶች ምን ይባሉ ነበር?

ሀ- መሳፍንት።

10. እግዚአብሔር እስራኤላውያን በመውደድና በመጠበቅ የጸናው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ታላቅ ሕዝብ የሚሆኑ ብዙ ዘሮችን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

ለ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ዘር አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።



- ቤተ መቅደሱም ቅድስተ ቅዱሳን የሚባል ሁለተኛ ክፍል ነበረው።

- የመገናኛው ድንኳን ሁለቱን ክፍሎች የሚለይ መጋረጃ ነበረው።

- ቤተ መቅደሱም እንዲሁ ሁለቱን ክፍሎች የሚለይ መጋረጃ ነበረው።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነና ኃጢአትን ሁሉ ስለሚጠላ ሊቀካሕኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው መቼ መቼ ነበር?

- በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነና ኃጢአትን ስለሚጠላ ሊቀ ካሕኑ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ምን ያደርግ ነበር?

- የእንስሳትን ደም በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ይረጭ ነበር።

- እግዚአብሔር ሊቀ ካሕኑ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ የረጨውን ደም ሲመለከት ምን ያደርግ ነበር?

- እግዚአብሔር ለቀጣዩ ተጨማሪ ዓመት የተሻለ መሥዋዕት እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ሕዝቡን በኃጢአቱ ከመቅጣት ይቆጠብ ነበር።

- የእንስሳቱ ደም የሰዎችን ኃጢአት ማስወገድ ይችል ነበር?

- አይችልም።

- የእንስሳቱ ደም የሰዎችን ኃጢአት ማስወገድ የማይችለው ለምንድን ነው?

1- ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ እንዲሠራ አዘዘ።

- ልክ አባቱ ንጉስ ዳዊት እንደነገረው ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤትን ሠራ።

- ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ያሠራው ቤት ስሙ ቤተ መቅደስ ይባላል።

- ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ከተማ ቤተ መቅደስ ሠራ።

- የኢየሩሳሌም ከተማ ብዙ እስራኤላውያን በሚኖሩበት በከነዓን ምድር ትልቅ ከተማ ነበረች።

- ከእስራኤል ጠላቶች ጥቃት ለመከላከል የኢየሩሳሌም ከተማ በትላልቅ የድንጋይ አጥሮች የተከበበች ነበረች።

- ሰሎሞን ለእግዚአብሔር የሠራው ቤተ መቅደስ እስራኤላውያን በበረሃ ለእግዚአብሔር የሠሩትን ድንኳን ይመስላል።

- ሰሎሞን ለእግዚአብሔር የሠራው ቤተ መቅደስ እስራኤላውያን በበረሃ ለእግዚአብሔር ከሠሩት የማደሪያው ድንኳን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነበር?

- የማደሪያው ድንኳን ቅድስት የሚባል የመጀመሪያ ክፍል ነበረው።

- ቤተ መቅደሱም ቅድስት የሚባል የመጀመሪያ ክፍል ነበረው።

- የመገናኛው ድንኳን ቅድስተ ቅዱሳን የሚባል ሁለተኛ ክፍል ነበረው።



ሐ- ምክንያቱም እግዚአብሔር መልእክቱን መጽሐፍ ቅዱስን በእስራኤላውያን ዘር በኩል ሊልክ ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

11. የመጨረሻው የእስራኤላውያን መስፍን ማን ነበር?

ሀ- ሳሙኤል።

12. ሳሙኤል ከመሞቱ በፊት እስራኤላውያን ሳሙኤል ምን እንዲያደርግላቸው ጠየቁት?

ሀ- እስራኤላውያን ሳሙኤል የሚመራቸውን ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ጠየቁት።

13. በዚህ ጥያቄ ሳሙኤል ያዘነው ለምን ነበር?

ሀ- ሳሙኤል ያዘነው፥ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዲሆን አለመፈለጋቸውን ስለ ተረዳ ነው።

- እግዚአብሔር ሳዖልን የመጀመሪያ የእስራኤላውያን ንጉሥ እንዲሆን መረጠው።

- እግዚአብሔር ሳዖልን መረጦ እንዲታዘዘው ቢፈልግም ሳዖል ግን በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀ።

- ስለዚህ ሳሙኤል እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ንጉሥ እንዲሆን ሌላ ሰው መምረጡን ለሳዖል ነገረው።

1ኛ ሳሙኤል 13፡13-14

13- ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ «የማይገባህን አደረግህ፤ አምላክህ እግዚአብሔር የሰጠህን ትእዛዝ አልጠበቅህም፤ ጠብቀኸው ቢሆን ኖሮ፣ መንግሥትህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም ባጸናልህ ነበር፤

14- አሁን ግን መንግሥትህ አይጸናም፤ እነሆ፣ እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሚሆንለት ሰው አግኝቶአል፤ አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመጠበቅህም፣ እርሱን የሕዝቡ መሪ አድርጎ መርጦታል።»

- ሳዖል በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ጊዜ ቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠው ማንን ነበር?

- ዳዊትን።

- እግዚአብሔር ሁለተኛው የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ዳዊትን መረጠው።

1ኛ ሳሙኤል 16፡1 & 13

1- እግዚአብሔር ሳሙኤልን፣ «በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳዖል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው? ወደ ቤተ ልሔም ሰው ወደ እሴይ ስለምልክህ፣ ዘይት በቀንድ ሞልተህ ሂድ፤ ከልጆቹ አንዱ ንጉሥ ይሆን ዘንድ መርጬዋለሁ» አለው።

13- ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ ፊት ቀባው። ከዚያ ቀን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኀይል መጣ።

- ሳዖል ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ሁሉ ዳዊትን ንጉሣቸው ሊያደርጉት መጡ።

2ኛ ሳሙኤል 5፡1-4



1ኛ ዜና 22፡5-6

5- ዳዊትም፣ «ልጄ ሰሎሞን ወጣት ነው፤ ልምድም የለውም፤ ለእግዚአብሔር የሚሠራው ቤተ መቅደስ ደግሞ እጅግ የሚያምር፣ በአሕዛብም ሁሉ ዘንድ ዝናው የተሰማና እጅግ የተዋበ መሆን አለበት፤ ስለዚህ ሁሉንም እኔ አዘጋጃለሁ» አለ። እንዳለውም ዳዊት ከመሞቱ በፊት በብዛት አዘጋጀ።

6- ከዚያም ልጁን ሰሎሞንን ጠርቶ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት እንዲሠራ አዘዘው።

- ዳዊት ከመሞቱ በፊት ልጁ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤት እንዲሠራ ነገረው።

- ከዚያ በኋላ ዳዊት ሞተ፤ ልጁም ሰሎሞን የእስራኤላውያን ንጉሥ ሆነ።

1ኛ ዜና 29፡26-28

26- የእሴይ ልጅ ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ነግሦ ነበር።

27- እርሱም በኬብሮን ሰባት ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት ዓመት፣ በአጠቃላይ አርባ ዓመታት ነገሠ።

28- ብዙ ዘመን፣ ባለጠግነትና ክብር ሳይጐድልበት ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ልጁ ሰሎሞን በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

- ሰሎሞን የእስራኤላውያን ንጉሥ ከሆነ በኋላ ምን አደረገ?

2ኛ ዜና 2፡1ሀ

2ኛ ሳሙኤል 7፡16

16- «ቤትህና መንግሥትህ በፊቴ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ዙፋንህም እንደዚሁ ለዘላለም የጸና ይሆናል።»

- እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ታላቅ የተስፋ ቃል ምን ነበር?

- እግዚአብሔር አዳኙን ከዳዊት ዘር እንደሚልክ ቃል ገባ።

- ይህ የተስፋ ቃል እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ከገባው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነበር።

- እግዚአብሔር ከዘላለም እስከዘላለም ንጉሥ የሚሆን አዳኝ ይልካል።

- እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ረስቶ ነበር?

- አልረሳም።

- እግዚአብሔር እኛን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ለማዳን የሚመጣውን አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ሁልጊዜም ያስታውሳል።

- ዳዊት ከመሞቱ በፊት የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ብዙ ቅድመ ዝግጅቶች አድርጎ ነበር።

- ከዚያም ዳዊት ልጁ ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤት እንዲሠራ ኃላፊነቱን ሰጠው።



1- የእስራኤል ነገዶች በሙሉ ወደ ኬብሮን ወደ ዳዊት መጥተው እንዲህ አሉ፤

2- «እነሆ፤ እኛ የዐጥንትህ ፍላጭ፣ የሥጋህ ቍራጭ ነን፤ ባለፈው ሳዖል በእኛ ላይ ነግሦ በነበረ ጊዜ፣ እስራኤልን በጦርነት የምትመራቸው አንተ ነበርህ፤ እግዚአብሔርም፣ ‘ሕዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፣ መሪያቸውም ትሆናለህ’ ብሎህ ነበር።»

3- ስለዚህም የእስራኤል ሽማግሌዎች በሙሉ ወደ ኬብሮን መጡ፤ ንጉሥ ዳዊትም ኬብሮን ላይ በእግዚአብሔር ፊት ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ እነርሱም ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ አነገሡት።

4- ዳዊት በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበረ፤ አርባ ዓመትም ገዛ።

- ሳዖልና ዳዊት የሚለያዩት እንዴት ነበር?

- ሳዖል ከእግዚአብሔር ተለይቶ በኃጢአት መወለዱን አላመነም ነበር።
- ዳዊት ግን ከእግዚአብሔር ተለይቶ በኃጢአት መወለዱን ያውቅ ነበር።

- ሳዖል እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ አላመነም ነበር።

- ዳዊት ግን እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ነበር።

- ሳዖል እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል አላመነም ነበር።
- ዳዊት ግን እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ያውቅ ነበር።

- ሳዖል እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል አላመነም ነበር።

- ዳዊት ግን እግዚአብሔር እርሱን ከሰይጣንና ከሞት ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ያውቅ ነበር።

- ዳዊት በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚረዱ ብዙ መዝሙሮችን ጽፏል።

- ዳዊት ዛሬ በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ብዙ የአምልኮ መዝሙሮችን ጽፏል።

- ዳዊት የእስራኤላውያን ንጉሥ ስለነበር ብዙ ገንዘብ ነበረው።

- ዳዊት የእስራኤላውያን ንጉሥ ስለነበር ከእንጨት ከድንጋይ ከወርቅና ከብር ትልቅ ቤት ሠራ።

- አንድ ቀን ዳዊት ስለራሱ ቤትና ስለ እግዚአብሔር ድንኳን ማሰብ ጀመረ።

2ኛ ሳሙኤል 7፡1-3

1- ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ ከተቀመጠና እግዚአብሔም በዙሪያው ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ካሳረፈው በኋላ፣ ነቢዩን ናታንን፣

2- «እነሆ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤተ መንግሥት ውስጥ እኖራለሁ፤ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል» አለው።

3- ናታንም፣ «እግዚአብሔር ካንተ ጋር ስለሆነ ያሰብኸውን ሁሉ አድርግ» አለው።

- ዳዊት የራሱን ቤት ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ ምን ለመሥራት ፈለገ?

- ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ፈለገ።

- እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት ይፈልጋል?



- አይፈልግም።

- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ስለሚገኝ የሚኖርበትን ቤት አይፈልግም።

- ምንም እንኳ እግዚአብሔር መኖሪያ ቤት ባይፈልግም ዳዊት ስለ እርሱ በማሰቡ እግዚአብሔር ተደሰተ።

- ታዲያ እግዚአብሔር ዳዊትን ምን አለው?

2ኛ ሳሙኤል 7፡12-13ሀ

12- ዕድሜህን ጨርሰህ ከአባቶችህ ጋር በምታንቀላፋበት ጊዜ፣ በእግርህ እንዲተካ ከአብራክህ የተከፈለ ዘር አስነሣለሁ፤ መንግሥቱንም አጸናለሁ።

13- ለስሜ ቤት የሚሠራ እርሱ ነው፤

- እግዚአብሔር በዳዊት አሳብ ቢደሰትም የእግዚአብሔርን ቤት የሚሠራው እርሱ አለመሆኑን እግዚአብሔር ለዳዊት ነገረው።

- የእግዚአብሔርን ቤት የሚሠራው ማን ነበር?

- የዳዊት ልጅ ሰሎሞን።

- ዳዊት በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ገባለት።

- እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ቃል ይህ ነው።